# የአሜሪካን እገር ኑሮ

የአሜሪካን ኑሮ እሯጭ ነኝ ያሰኛል፤
ጡንቻን አሰርቶ ልብን አስጨንቆ፤
አእምሮን አዝሎ ሳብ ያንጠፈጥፋል፤
ታዲያ ከነ አበበ ቢቂላ ማራቶን በምኑ ይለያል?

ማራቶን አድክሞ ሜዳልያ ቢያስገኝም፤
የአሜሪካን የኑሮ እሩጫ ግን ሽልማት የለውም።
ማራቶን እሯጮች ተከባብረው ኑሮዋቸው ሲሟላ፤
እና እሯጮቹ ግን ኪሳችን ተጉላላ።

ወጣት እያለን እንሩጠው እሩጠው እሩጭው፤
እድሜ ከገፋ ጡንቻ ከደከመ ጉልበት ከለገመ ልብ ከሰለቸው፤
አገሩ ከባድ ነው እንኳን እኛ፤
የኢትዮጵያም አህያ ቢመጣ የማይችለው።

ከ ኒኒ ለገሰ